# የወንጌል ብርሃን ቤተክርስቲያን በኦስሎ መሠረተ እምነትና መተዳደሪያ ደንብ

ኦስሎ፣ ኖርዌይ
2019

# መግለጫ

1. ስያሜ - 4 -
2. ዓላማ - 4 -
3. መሠረተ እምነት - 4 -
3.2 ስላሴ - 4 -
3.3 እግዚአብሔር አብ - 5 -
3.4 ኢየሱስ ክርስቶስ - 5 -
3.5 መንፈስ ቅዱስ - 5 -
3.6 አዲስ ፍጥረት/ደህንነት/ - 5 -
3.7 የውሃ ጥምቀት - 6 -
3.8 ቅዱስ ቁርባን - 6 -
3.9 ቅድስና - 6 -
3.10 የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት - 6 -
3.11 ፍርድ - 6 -
4. የመተዳደሪያ ደንብ - 7 -
4.1 የቤተ ክርስቲያን መዋቅር - 7 -
4.2 አስተዳደር - 7 -
4.3 ምልአተጉባኤ - 8 -
4.4 የመሪዎች ጉባኤ - 8 -
4.7 መጋቢ - 10 -
4.8 የመጋቢ ችሎታና ብቃት - 10 -
4.9 የመጋቢ ስራ ዝርዝርና ኃላፊነት - 11 -
4.10 ረዳት መጋቢ - 12 -
4.11 ወንጌላዊ - 12 -
4.12 የወንጌላዊ ችሎታና ብቃት - 13 -
4.20 የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ከሥራ መልቀቅ ወይንም የመገለል ሁኔታ - 16 -
4.21 የቤተክርስቲያን ሽማግሌ - 16 -
4.22 የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አመራረጥ - 17 -
4.23 የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የአገልግሎት ዘመን - 17 -

# 1. ስያሜ

1.1.1.1 ይህ መተዳደሪያ ደንብ በሃገረ ኖርዌይ፣ ኦስሎ ከተማ የምትገኘው የወንጌል ብርሃን ቤተክርስቲያን የእምነት መግለጫና መተዳደሪያ ደንብ ተብሎ ይታወቃል፡፡

# 2. ዓላማ

2.1.1.1 ሰዎች ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት በእምነት እንዲቀበሉና ከዚያም የተነሳ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲወርሱ የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት መስበክና ማስተማር፡፡

2.1.1.2 የክርስቲያኖች እምነትና ታማኝነት እንዲጠነክር በፀሎት፣በእግዚአብሔር ቃልና በምክር የታነፀ ሕይወት እንዲኖራቸውና ከዚህም የተነሳ ሰዎች በመንፈስቅደስ ኃይል የታጠቀ ሕይወት በመምራት በሕይወታቸው ጌታኢየሱስን እያንፀባረቁ እንዲኖሩ መደገፍ፡፡

2.1.1.3 ጥሪ ያላቸውን አገልጋዮች የአገልግሎት ጸጋቸውንና ፍሬያቸውን በመመልከት በጥሪያቸው መሠረት ወደ አገልግሎት ማሰማራት፡፡

2.1.1.4 አማኞችን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ማሰልጠንና ማሰለፍ፡፡

2.1.1.5 አማኞችን በአብ በወልድ በመንፈስቅዱስ ስም በማጥመቅና ደቀመዛሙርት ማድረግ፣ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ” ብሎ ያዘዘውን ቃል በተግባር ማዋል፡፡

2.1.1.6 የክርስቶስ አካል ከሆነችው ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ጋር መንፈሳዊ ሕብረትና አንድነት ማድረግ፡፡

2.1.1.7 በቤተክርስቲያንና በህብረተሰባችን ውስጥ በሚከናወኑ ማኅበራዊነክ ጉዳዮች ላይ በንቃት በመሳተፍ ማከናወን፡

# 3. መሠረተ እምነት

## 3.1መጽሐፍ ቅዱስ-

3.1.1 የብሉይ ኪዳን 39 መጻሕፍትና አዲስኪዳን 27 መጻሕፍት በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ የእግዚአብሔር ቃል በሰው እምነትና ሕይወት ላይ የመጨረሻ ሥልጣን ያለው የቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት መሠረት እርሱ ብቻ እንደሆነ እናምናለን፡፡ 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16፣ ዕብራውያን 4፥12 ፣ 2ኛጴጥሮስ 1፥20-21 ::

## 3.2 ስላሴ

3.2.1 እውነተኛውና ዘላለማዊው አምላክ፣ እንደ ቅዱስ ቃሉ ትምህርት መሰረት ፣ ራሱን በአንድ አምላክነቱ እንዲሁም በሶስት አካልነቱ እንደገለጠ እናምናለን። ስለዚህ የእግዚአብሄርን የመለኮት አንድነትና የአካል ሶስትነት እናምናለን።

## 3.3 እግዚአብሔር አብ

3.3.1.1 ዘላለማዊ፣ በማይወሰን፣ፍጹም፣ራሱን በመንፈስቅዱስ በሚገልጥ ሁሉን በሚችል በሁሉ ቦታ በሚገኝ ሁሉን በሚያውቅ በማይለዋወጥ በአንድ አምላክ፣የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን፡፡ዘፍጥረት 1፥1-31፣ ዘፍጥረት 2፥7፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 8፥6፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 6፥18፣ 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥ 17፡፡

## 3.4 ኢየሱስ ክርስቶስ

3.4.1.1 የእግዚአብሔር አብ ልጅ መሆኑን፣በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም መወለዱን፣ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን፣ስለ ሐጢአታችን በመስቀል ላይ የተሰቃየና የሞተ የተቀበረ በሶስተኛው ቀን ከሞት በአካል ተነስቶ ለሰዎች ተገልጦ በክብር ወደሰማይ ያረገ መሆኑን፣ አሁንም በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ዘወትር ለእኛ እንደሚማልድልን፣ዳግመኛም በታላቅ ክብርና ሥልጣን እንደሚመለስ እናምናለን፡፡ማቴዎስ 16፥16፣ የሐዋሪያትሥራ 5፥30-31፣ማቴዎስ 1፥23፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥3-8፣የሐዋሪያትሥራ 1፥9-11 ፡፡

## 3.5 መንፈስ ቅዱስ

3.5.1.1 አካላዊ ማንነት ባለዉና መለኮት በሆነው በመንፈስቅዱስ እናምናለን።ይህም እውነት በመፅሓፍቅዱስ ዉስጥ በተለያዩ መንገዶች ተረጋግጦአል። 1ኛ ጢሞ 4፥1 ፣ራዕ 2፥7፣ ሉቃ 12፥12፣ዮሐ 14፥26፣ሐዋ 15፥28፣ሐዋ13፥ 2፣ኢዮ 26፥13፣33፥4፣መዝ 104፥30፣1ኛ ቆሮ 2፥10-11፣ኢሳ 40፥13-14 ወ.ዘ.ተ

3.5.1.2 አጽናኝ፣አስተማሪ ወደ እውነት የሚመራ መንፈሳዊ አባቶችን ነቢያትን ሐዋርያትን ያንቀሳቀሰና የመራ፣ በአማኞችም ውስጥ አድሮ መንፈሳዊ ስጦታዎችና ኃይልን በማከፋፈል ቤተክርስቲያንን እንደሚያንጽ፣ ዓለምንም ስለኃጢአት፣ስለጽድቅና ስለፍርድ እንደሚወቅስ እናምናለን፡፡የሐዋርያትሥራ 2፥ 1-11፣ 2ኛጴጥሮስ 1፥21፣የሐዋሪያትሥራ 1፥8፣ 1ኛቆሮንቶስ 12፥4-11፣ኤፌሶን 4፥11-12፤

3.5.1.3 አማኞች በመንፈስቅዱስ ኃይል እንደሚጠመቁ እናምናለን፡፡ማርቆስ 16፥17-18፣የሐዋርያትሥራ 10፥44-46፤

3.5.1.4 በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 መሠረት ዛሬም የመንፈስቅዱስ ሙሊትን አማኞች በፀሎትና በእምነት ሊቀበሉት እንደሚገባ ከክርስቶስ የተሰጠ ትዕዛዝ መሆኑን እናምናለን፡፡የሐዋርያትሥራ 1፥4-5፣ 2፥38-39፣ ኤፌሶን 5፥18 ፤

3.5.1.5 በሐዋርያት ዘመን እንደነበረ በዘመናችንም የመንፈስቅዱስ ስጦታዎች ለአማኞች እንደሚሰጥ እናምናለን፡፡ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥1-11፣ 12፥28-30፣ 7፥7፣13፥1-3፣ኤፌሶን 4፥11፣1ኛ ጴጥሮስ 4፥11 ፤

3.5.1.6 በዚህም ዘመን በቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን በማክበር በአማኞች ውስጥ ሆኖ እንደሚሠራ እናምናለን፡፡ዮሐንስ 16፥7-15 ።

## 3.6 አዲስ ፍጥረት/ደህንነት/

3.6.1.1 ሰው በመጀመሪያ ያለኃጢአት መፈጠሩን እናምናለን፡፡ይሁን እንጂ አዳም በፈቃደኝነት ኃጢአት ላይ በመውደቁ ምክንያት ከአዳም በኋላ የመጣ ሰው ሁሉ የኃጢአት ባህሪ ይዞ መወለዱን እናምናለን። ነገርግን ሰው ይህን ሃጢአተኝነቱን አውቆ፣የኢየሱስክርስቶስን የመስቀል ስራ አምኖ ከተቀበለና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኙና ጌታው አድርጎ ከተቀበለ፣ከመንፈስቅዱስና ከእግዚአብሔር ቃል የተወለደ አዲስ ፍጥረትና የእግዚአብሔር ልጅም መሆኑን እናምናለን፡፡ ዘፍጥረት 1፥26-28፣ ዘፍጥረት 3፥1-24፣ ሮሜ10፥9-10፣ ዮሐንስ1.12–13።

## 3.7 የውሃ ጥምቀት

3.7.1.1 በጌታችን ኢየሱስክርስቶስ ትዕዛዝ መሠረት አማኝ በአብ በወልድ በመንፈስቅዱስ ስም በውሃ እንደሚጠመቅ እናምናለን፡፡ ማቴ 28፥19

3.7.1.2 አንድ ክርስቲያን ለዚህ ዓለምና ለኃጢአት የሞተ፣ለፅድቅ ደግሞ ህያው መሆኑን በእግዚአብሔርና በቅዱሳን ፊት የሚያረጋግጥበት ምሳላያዊ ተግባር መሆኑን ቤተክርስትያን ታምናለች፤ በዚሁም መሠረት የአዋቂ ጥምቀትን (አንድ አማኝ ተምሮና አውቆ የሚያደርገዉን) በተግባር ታውላለች፡፡

3.7.1.3 ቤተክርስቲያንዋ በምታዘጋጀው ትምሕርት መሠረት የውሃ ጥምቀት ይከናወናል፣ሮሜ 6፥1-6

3.7.1.4

## 3.8 ቅዱስ ቁርባን

3.8.1.1 በህብስትና በወይን ጭማቂ የሚዘጋጀውን ቅዱስ ቁርባን፣ ሥለ እኛ የሆነዉን የጌታችንን የመድኃኒታችንን ስቃይና ሞት የምናስብበትና ሞቱንም የምንናገርበት ቅዱስ ሥርዓት መሆኑንና ስለዚህም ጌታ እስኪመጣ ድረስ በቤተክርስቲያን መከናወን ያለበት መሆኑን እናምናለን፡፡ማቴዎስ 26፥26-28፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፥23-30።

## 3.9 ቅድስና

3.9.1.1 የክርስቲያኖች ሁሉ ጥሪ እንደሆነ፣ይህም ማለት ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝና ለእግዚአብሔር ተለይቶ በመኖር መንፈሳዊ ፍሬ በማፍራት ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ማድረግ እንደሆነ እናምናለን፡፡ኤፌሶን 2፥10፣ 1ኛ ጴጥሮስ 1፥15፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 7፥1፣ዮሐንስ 15፥1-11።

## 3.10 የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት

3.10.1.1 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር እንደገና እንደሚመጣ፣ በእርሱ አምነው የሞቱት ቀድመው እንደሚነሱ ሕያዋን የሆኑት ደግሞ እርሱን ለመቀበል እንደሚነጠቁ እናምናለን። 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥51-52፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 4፥15-17።

## 3.11 ፍርድ

3.11.1.1 ጻድቃን ከጌታ ጋር ለዘልዓለም በሕይወት እንደሚኖሩ ኃጢአተኞች ግን ከእግዚአብሔር ፊት ተለይተው በገሃነምእሳት ለዘለዓለም እንደሚሰቃዩ እናምናለን፡፡ ራዕይ 7፥9-15፣ 19፥11-14፣ ለቃስ 13፥23-30፣ ማቴዎስ 25፥31-46፣ ራዕይ 20፥10-15፣ ማቴዎስ 24፥38-44፣ 25፥1-13፣ የሐንስ 14፥2-4፡፡

# 4. የመተዳደሪያ ደንብ

## 4.1 የቤተ ክርስቲያን መዋቅር




4.1.1 **ጠቅላላ ጉባኤ ፡ ሲባል የቤተክርስቲያን ጠቅላላ አባላት ጉባኤ ማለት ነው።**

4.1.1.1 በቤተክርስቲያኒቱ ጉዳዮችና ውሳኔዎች ላይ የቤተክርስቲያን ጠቅላላ አባላት ጉባኤ የመጨረሻው ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፡፡ ይህም የሚሆነዉ በአብይ ጉዳዮች ላይ 60 በመቶ አባላት በተገኙበት ከተገኙትም 75 በመቶዉ የተስማሙ ሲሆን ነዉ። እነዚህም አብይ ጉዳዮች የቤተክርስቲያንን ህልዉናን ጉዳይ የሚመለከት፣ የቤተክርስቲያንን ንብረት የሚመለከት፣ የቤተክርስቲያንን መተዳደሪያ ደንብ በሚመለከት እና እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው እነዚህ ጉዳዮች በመሪዎች ጉባኤ ከታመነባቸዉ ለጠቅላላ አባላት ጉባኤ ይቀርባሉ

4.1.1.2 ምልአተጉባኤ፡ አባላት ለስብሰባ የሚጠሩት ቢያንስ ከስብሰባው ቀን አንድ ወር ያህል ጀምሮ በማስታወቂያና በሌሎች መንገዶች ሁሉ (ለምሳሌ በቤተክርስቲያን ድህረገጽ) የስብሰባው ቀን ተነግሮ እንዲሁም ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት የስብሰባው አጀንዳ ተሰጥቶ ነው። በዚህ ሁኔታ ተጠርተው ሁሉም ባይገኙ፣ ግን በተገኙት አባላት ውሳኔ ሊተላለፍ ይችላል፣ ይህም ከተገኙት መካከል ሶስት አራተኛው ከተስማሙ ይሆናል። የሚሰጡ ውሳኔዎች በሁሉም አባላት ስምምነት መወሰድ ቢኖርባቸውም አስገዳጅ ሁኔታ ግን ሲፈጠር ግን በድምጽ ብልጫ ይሆናል።

## 4.2 የመሪዎች ጉባኤ

4.2.1.1 የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች ጉባኤ የተሾመውን መጋቢና በአባላት ጉባኤ የተመረጡ ሽማግሌዎችን ያጠቃለለ ይሆናል፡፡

4.2.1.2 ቤተክርስቲያኒቱ በመሪዎች ጉባኤ ትመራለች።

4.2.1.3 የመሪዎች ጉባኤ በቤተክርስቲያኒቱ መንፈሳዊና አስተዳደር-ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አመራር ይሰጣል።

4.2.1.4 መጋቢው ከመንግስት ጋር በ"ፊልከስማነን" በኩል ባለው ግንኙነት ተጠሪ ነው፣ በመንግስት በኩልም የቤተክርስቲያኒቱ "forstander" በመባል ይታወቃል።

4.2.1.5 ማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ አገልግሎት በመጋቢ ኃላፊነት ስር ሆኖ፡ የተቀሩት የመሪዎች ጉባኤ አባላት ለአገልግሎቱ ስኬት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

4.2.1.6 ከተመራጭ ሽማግሌዎች መካከል አንድ ተወካይ በ"ብሮነይሱንድ" በኩል ለሚኖረው የመንግስት ግንኙነት ተጠሪ ይሆናል፣ ይኸውም ገንዘብ ነክ የሆኑ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ያካተተ ስለሆነ ነው።

4.2.1.7 በመሪዎች ጉባኤ ሥር ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ከበድ ባሉና ትልልቅ ዉሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ የምክር ድጋፍ የሚሰጥ ኮሚቴ ሊቋቋም ይችላል፣ ይኸውም ከአገልግሎት ክፍል መሪዎችና ከአባላት መካከል በመሪዎች ጉባኤ የተሰየሙ ወገኖችን ያቀፈ ይሆናል።

4.2.1.8 በመሪዎች ጉባኤ ሥር ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ረዳት አስተዳደሪ ሊመደብ የሚችል ሲሆን ጉባኤው በሚሰጠው የሥራ ዝርዝር መሰረት አስተዳደራዊ ጠባይ ያላቸውን ስራዎች ያከናውናል፡፡

## 4.3 የመሪዎች ጉባኤ የስራ ዝርዝርና ሃላፊነት

4.3.1.1 የቤተክርስቲያን መሪዎች ጉባኤ የቤተክርስቲያኒቱን አመታዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ በአባላት ጉባኤ በማጸደቅ በተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ አፈጻጸሙንም ይገመግማል፡፡

4.3.1.2 ለሁሉም አገልግሎት ክፍሎች የሥራ ዝርዝርና የአሰራር መመሪያ በጽሑፍ ይሰጣል፡፡

4.3.1.3 በቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያገለግሉትን የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ይሾማል፣ ደመወዝን እና ሌላም ድጎማን በተመለከተ ውሳኔ ያሳልፋል፡፡

4.3.1.4 የቤተ ክርስቲያኒቱን የሒሳብ ይዘት ያካተተ ጠቅላላ ሪፖርት በዓመት ሁለት ጊዜ አጠናቅሮ ለጠቅላላው ጉባዔ ያቀርባል፡፡

4.3.1.5 የቤተ ክርስቲያን ሒሳብ የሚመረምር ሒሳብ መርማሪ (ኦዲተር) አስመድቦ ሒሳቡን በዓመት አንድ ጊዜ ኦዲት የማስደረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

4.3.1.6 ከመሪዎች ጉባኤ ውስጥ የተወከሉ ሁለት ሽማግሌዎች በጣምራ የቤተክርስቲያናን ሒሳብ ያንቀሳቅሳሉ፤ ያስተዳድራሉ፤ የቤተ ክርስቲያኒቷን የገንዘብ አያያዝ በሚመለከት እቅድ ያወጣሉ፣በዚህ እቅድ መሰረት ስራቸዉን ያካሂዳሉ።

4.3.1.7 ማንም አባል ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር የጎደለው ተግባር ሲፈፅም የመሪዎች ጉባኤ በሚመለከተው የቤተክርስቲያን አባል ላይ እንደ አስፈላጊነቱ የዲሲፕሊን ርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለበት፡፡

4.3.1.8 የመሪዎች ጉባኤ አባላት ቤተክርስቲያኒቱን የሚመለከቱ ማንኛውንም ጉዳዮች ተነጋግሮ ለመወሰን በየወቅቱ ይሰበሰባሉ፡፡ አስቸኳይ ሁኔታ ሲፈጠር ደግሞ ጉባዔው ከዚህ ውጪ ሊሰበሰብ ይችላል።

## 4.4 የመሪዎች ጉባኤ አባላት ኃላፊነት

### 4.4.1 ሰብሳቢ

4.4.1.1 የመሪዎች ጉባኤ የራሱን ሰብሳቢ ይመርጣል።

4.4.1.2 የመሪዎች ጉባኤን ስብሰባ ይመራል።

4.4.1.3 የአባላት ጉባኤ ሲጠራ ስብሰባዉን ይመራል።

4.4.1.4 የቤተ ክርስቲያኒቱን ማህተም ይይዛል፣ በተጨማሪም የቤተክርስቲያኒቱ ህጋዊ ሰነዶች በአግባብ መያዛቸውን ያረጋግጣል።

### 4.4.2 ምክትል ሰብሳቢ

4.4.2.1 ሰብሳቢው በሌለበት የሰብሳቢዉን ስራ ይሸፍናል።

4.4.2.2 ሰብሳቢዉን በሚያስፈልገው አገልግሎት ሁሉ ይረዳል።

4.4.2.3 የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደራዊ ስራ ይከታተላል።

### 4.4.3 ፀሓፊ

4.4.3.1 የመሪዎች ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ፣ የአገልጋዮች የጋራ ስብሰባ፣ የአባላት ጠቅላላ ስብሰባና የመሳሰሉት የቤተክርስቲያን ስብሰባዎች በሚደረጉበት ጊዜ ቃለጉባዔዎችን፣ ውሳኔዎችን፣ ትዕዛዞችንና ሀሳቦችን በጽሑፍ አስፍሮ (አጠናቅሮ) በመዝገብ ወይም በሠነድ ያስቀምጣል፡፡

4.4.3.2 የተያዙ አጀንዳዎችን መፈጸም በመከታተል ለሽማግሌዎች ጉባኤ ያስታዉሳል።

4.4.3.3 ሰብሳቢውና ም/ ሰብሳቢው በሌሉበት ጊዜ የመሪዎች ጉባዔ ስብሰባ ይመራል፣

### 4.4.4 ሒሳብ እና ንብረት ሃላፊ

4.4.4.1 ቤተ ክርስቲያኒቱ በራሷ ሥም የባንክ አካውንት ያላት ሲሆን፣ ባንኩም እዚሁ ሃገር ውስጥ ይሆናል። አካውንቷም የሚንቀሳቀሰውና የሚተዳደረው በቤተ ክርስቲያኗ የመሪዎች ጉባኤ ዋና ሰብሳቢ እና በንብረትና ፋይናንስ ኃላፊ አማካኝነት ይሆናል። በሥሩ ገንዘብ ያዡንና ሒሳብና ንብረት ክፍልን ይይዛል።

4.4.4.2 ገንዘብ ያዥ (ካሸር)፡ - የቤተ ክርስቲያኒቱ ገንዘብ ተቀማጭነቱ ባንክ ቤት በመሆኑ፣ እዚህ ላይ ገንዘብ ያዥ (ካሸር) የሚለው ዕለታዊ ተንቀሳቃሽ ገንዘብ (petty cash) የሚይዘውን ሰው ይወክላል፤

4.4.4.3 የቤተክርስቲያኒቱን የሒሳብ ደብተር በሒሳብ አያያዝ ደንብ መሠረት ይይዛል፡፡ የቤተክርስቲያኒቱ ገንዘብ የሚንቀሳቀሰው የመሪዎች ጉባዔ ባፀደቀው የሒሳብና ንብረት መመሪያ መሠረት ይሆናል፤ገንዘብ ወጪ የሚሆነው በሁለት አባል ፊርማ ሲሆን ሒሳብና ንብረት ሹምና የመሪዎች ጉባኤ ዋና ሰብሳቢ ጣምራ ፊርማ ነው፡፡ በየዓመቱ በሚወጣው በጀት መሠረት ገንዘብ ለተገቢው አገልግሎት ይውላል።

4.4.4.4 የቤተክርስቲያኒቱ ካፒታልና ሌሎች ሒሳብ-ነክ ሰነዶች በጥንቃቄ መያዛቸውን ይከታተላል፡፡

4.4.4.5 በመሪዎች ጉባኤ ትዕዛዝ መሠረት በቤተክርስቲያኗ ስም ገንዘብና የተለያዩ ንብረቶችን በተገቢው ቦታ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

4.4.4.6 የቤተክርስቲያኒቱ ወጪዎች እንደአስፈላጊነታቸው በተገቢው ቦታ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፡ ፡

4.4.4.7 በመሪዎች ጉባኤ ሲጠየቅ የሒሳብ መዝገቡ ለምርመራ እንዲቀርብ ያመቻቻል፡፡

4.4.4.8 በመሪዎች ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች የሥራ ኃላፊነቶች በታማኝነት ያከናውናል፡፡

4.4.4.9 በዓመት ሁለት ጊዜ በሚደረገው የአባላት ጠቅላላ ስብሰባ የቤተክርስቲያኒቱን ገንዘብ ነክ ሪፖርት የሚያቀርብ ሲሆን፣ በሒሳብ መርማሪዎች(ኦዲተሮች) አስመርምሮ ደግሞ አንድ ጊዜ ያቀርባል፡፡

## 4.5 መጋቢ

4.5.1.1 መጋቢ ማለት አባላቱን የሚጠብቅ፣ የእግዚአብሔር ቃልን የሚመግብ፣የእግዚአብሄርን መንጋ የሚንከባከብና የሚያሳድግ መንፈሳዊ መሪ ነው፤

4.5.1.2 ከቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር በመሆን የቤተክርስቲያን ራእይ ዝግጅትና እቅድ ይመራል፤ በስራ ይተገብራል።

4.5.1.3 የመጋቢ አጠቃላይ አገልግሎት የሚከተሉትን ያካትታል ፦ እረኛ፣ መሪ አገልጋይ፣ አስተማሪ ሰባኪ፣ አነቃቂ፣ ደጋፊ፣ አጽናኝ፣ አስተባባሪነት ወዘተ።

4.5.1.4 የቤተክርስቲያን መጋቢ በሽምግልና ጉባዔው አቅራቢነት በቤተክርስቲያኑ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ይሾማል፡፡ ይህም የሚሆነዉ በቤተ ክርስቲያን አባላት 75 በመቶዉ ጠቅላላ ጉባኤ ስምምነት አማካኝነት ነዉ።

4.5.1.5 የመጋቢው ተጠሪነት ለቤተክርስቲያኒቱ ጠቅላላ አባላት ጉባኤ፤ እንዲሁም ለቤተክርስቲያን መሪዎች ጉባኤ ይሆናል።

## 4.6የመጋቢ ችሎታና ብቃት

4.6.1.1 በመጋቢነት ለማገልገል መለኮታዊ ጥሪና ጸጋ ያለው፣ኤፌሶን 4፥11

4.6.1.2 በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተጠቀሱትን የመጋቢነት መስፈርቶች የሚያሟላ፣1ኛ ጢሞ 3፥1-7፣ቲቶ 1፥6-9፣ 1ኛ ጴጥ 5፥1-4፣

4.6.1.3 ለታላቁ እረኛ ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ የሆነና ለመንጋው ርኅራኄና ፍቅር በማሳዬት በምሳሌነት የሚመላለስ፣

4.6.1.4 ጤናማ መንፈሳዊ ትምህርት በመስጠት ምዕመናንን የመንከባከብና የማሳደግ ብቃት ያለው፣የሐዋርያትሥራ 20፥28፣ 1 ጢሞቴዎስ 3፥1) ፤

4.6.1.5 በመንፈስቅዱስ የተሞላና በቅዱሳን የተመሰከረ አገልግሎት ያለው፣2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥1-5

4.6.1.6 ራሱን ለአገልግሎት አሳልፎ የሰጠና የቤተክርስቲያንን አንድነት የሚጠብቅ፣ዮሐንስ 10፥11፣

4.6.1.7 ምእመናንን በመጎብኘት መልካም ተሞክሮ ያለውና በተጨማሪም ለታመሙና በተለያየ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች የጸሎት፣ የማጽናናትና የምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚተጋ፣

4.6.1.8 ወንጌልን በትጋት የሚመሰክርና ላልዳኑ ነፍሳት ሸክም ያለው፣ማቴ 18፥12-14፣የሐዋ ሥራ 6፥1-5

4.6.1.9 በቤተክርስቲያኗ የእምነት መግለጫ የሚያምንና የመተዳደሪያ ደንቡንም የሚያከብርና የሚያስከብር፣

4.6.1.10 ከሌሎች ጋር በጋራ ለመስራት ተሰጥኦ ወይም ተነሳሽነት ያለው፣

4.6.1.11 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመደበኛ የስራ ሰአት ውጭ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ፣

4.6.1.12 አገልግሎቱ ስለሚያስከፍለው ዋጋ ግንዛቤ ያለውና መስዋእትነት ለመክፈል የተዘጋጀ፣

4.6.1.13 ቤተሰብ ካለው በእግዚአብሄር ቃል አስተምህሮ መሰረት ቤተሰቡን ከመምራትና ከመንከባከብ አኳያ መልካም ምስክርነት ያለው፣

4.6.1.14 ቢቻል ቀደም ሲል በተመሳሳይ አገልግሎት ያገለገለና ካገለገለበት ወይም ካለበት ቤተ ክርስቲያን የሕይወትና የአገልግሎት ምስክርነት ማቅረብ የሚችል፣

4.6.1.15 በስነመለኮት ትምሕርት ቤት የተማረ፡፡

## 4.7 የመጋቢ ስራ ዝርዝርና ኃላፊነት

### 4.7.1 የአምልኮ አገልግሎት

4.7.1.1 የቃል አገልግሎት፤ በስብከትና በትምህርት አባሎችን በመንፈሳዊ ህይወትማሳደግ፣ ለአገልግሎት ማብቃትና ማደራጀት

4.7.1.2 የጸሎት አገልገሎት፣የተለያዩ የጸሎት መድረኮች ማደራጀትና መምራት

4.7.1.3 የዝማሬ አገልግሎቶችን ማደራጀትና ማጠናከር፣

### 4.7.2 የአመራር ኃላፊነቶች

4.7.2.1 ከመሪዎች ጋር በመሆን ዓመታዊ እቅድ እና በጀት በአመት አንድ ጊዜ ማዘጋጀት፣

4.7.2.2 እንዲሁም የስራ አፈጻጸም የጽሁፍ ሪፖርት በዓመት ሁለት ጊዜ ለመሪዎች ጉባኤ ያቀርባል

4.7.2.3 ቤተክርስቲያኒቱ ህብረት ካላት ከሌሎች አብያተክርስትያናትና ህብረቶች ጋር ያለውን ግንኙነት በሃላፊነት ይከታተላል፤

4.7.2.4 ለአገልግሎት የተረከባቸውን የቤተክርስቲያኒቱን ንብረቶች በአግባቡ መያዝ።

### 4.7.3 ቅዱሳንን የማብቃት አገልግሎቶች

4.7.3.1 ጤናማና ተመጣጣኝ መንፈሳዊ ትምህርት በመስጠት ምዕመናንን መንከባከብ ማሳደግና ለአገልግሎት ማብቃት፣

4.7.3.2 የተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎች ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ያደራጃል፣ ያስተምራል፤ የአባላትን ጸጋ በመለየት በተለያዩ አገልግሎት ክፍሎች መመደብና ማበረታታት፤

4.7.3.3 ለአገልግሎት ክፍሎች እድገትና ጥንካሬ የሚረዱ መንፈሳዊ ስልጠናዎችን ማመቻቸት/ማካሄድ፣

4.7.3.4 ደቀመዝሙርነት ማስተማርና ለአገልግሎት ማብቃት፣

4.7.3.5 የጉብኝት አገልግሎት - የታመሙት መጎብኘት፣ ያዘኑት ማጽናናት፣ የደከሙትን ማበረታታት፣

4.7.3.6 የጸጋ ሰጦታዎች እንዲገለጡና እንዲጎለብቱ ማበረታታት

### 4.7.4 በየጊዜው የሚከናወኑ አገልግሎቶች

4.7.4.1 ከመሪዎች ጋር በተስማሙበት መሰረት ፕሮግራም ማዘጋጀት በሀላፊነት መምራት ከቤተክርስቲያን ውስጥና ከሌላ ቦታ አስተማሪዎች ሰባኪዎችንና ዘማሪዎችን መመደብና መጋበዝ፤ የኮንፈረንስ አገልጋዮች ምርጫ በመሪዎች ጉባኤ የሚከናወን ይሆናል።

4.7.4.2 በተመደበለት የስራ ሰዓት ዘወትር ቤተክርስቲያን በመገኘት ጸሎት ምክርና ሌላም መንፈሳዊ አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች በትጋት መስጠት፣

4.7.4.3 ሳምንታዊ የጉብኝት ፕሮግራሞችን በማውጣት በተናጠልም ሆነ ከመሪዎች ጉባኤ አባላት ጋር በማቀናጀት ምእመናንን መጎብኘት፣ ማፅናናትና መጸለይ ወዘተ፣

4.7.4.4 በእሁድ አምልኮ ፕሮግራምና በሌሎች የቤተክርስቲያኒቱ መደበኛ ፕሮግራሞች ላይ ፕሮግራም መሪዎችና በቃል የሚያገለግሉ ወገኖችን ምደባ ማከናወን።

4.7.4.5 ለታመሙና በተለያየ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች የጸሎት፣ የማጽናናትና የምክር አገልግሎት በግል ወይም ሌሎችን በመላክ ማከናወን፣

4.7.4.6 የአገልግሎት ክፍሎችን አመታዊ እቅድ ተግባራዊነት በቅርብ መከታተል፣ ለእቅዶች ተፈጻሚነት የቅርብ ድጋፍ ማድረግ፣በተጨማሪም ከአገልግሎት ክፍል መሪዎችና አባላት ጋር መደበኛ የውይይትና የጸሎት ፕሮግራሞች ማካሄድ፣

4.7.4.7 የቤተክርስቲያን አባላት በቤተክርስቲያን መደበኛ የጸሎት ፕሮግራሞችና በመጽሀፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት፣

4.7.4.8 የአገልግሎት ክፍሎች የስራ ድርሻቸውን ማዘጋጀት እንዲችሉ ደጋፍን መስጠት፣

4.7.4.9 በቤተክርስቲያኒቱ የአገልግሎት ክፍሎች መካከል ያለው መቀራረብ እንዲጎለብት አስተዋጽኦ ማድረግ፣

4.7.4.10 ከወንጌላዊው ጋር በቅርበት በመስራት የወንጌል ስርጭት አገልግሎትን ማካሄድ።

4.7.4.11 የቤተክርስቲያንን የመንፈስ አንድነት መጠበቅ፣

4.7.4.12 የተለያዩ የቤተክርስቲያን ስርአቶችን ማከናወን - የጌታ እራት፣ የጋብቻ፣ የጥምቀት፣ የቀብር እና ለአገልግሎት የመቀባት ስነስርአት ማከናወን፣

4.7.4.13 እንደ አስፈላጊነቱ በቤተክርስቲያን የመሪዎች ጉባኤ የሚወሰኑቱን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን፣

## 4.8 ረዳት መጋቢ

4.8.1 የመሪዎች ጉባኤ እንደ አስፈላጊነቱ ረዳት መጋቢ በአባላት ጉባኤ ስምምነት ይሾማል፡፡ ተፈጻሚነቱም በ 4.5 መሰረት ይሆናል።

4.8.2 መጋቢው በሌለበት ረዳት መጋቢ ሆኖ የሚያገለግለው በ4.6 የተጠቀሱትን አገልግሎቶች ይፈጽማል፡፡ ረዳት መጋቢው ከሌለ የመሪዎች ጉባዔ ስራዉን በመከፋፈል ይህንን አገልግሎት ይፈጽማሉ፡

4.8.3 ረዳት መጋቢ ተጠሪነቱ ለዋናው መጋቢ ይሆናል

## 4.9 ወንጌላዊ

4.9.1 ወንጌላዊ ማለት መልካሙን ዜና ማለትም ወንጌልን ላልዳኑ ነፍሳት ሁሉ በትጋት የሚመሰክርና የእግዚአብሔር መንግስት እንዲሰፋ የሚጥር አገልጋይ ማለት ነው፤

4.9.2 ወንጌላዊ በመሪዎች ጉባኤው አቅራቢነት በቤተክርስቲያኑ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ይሾማል፡፡ ይህም የሚሆነዉ በቤተ ክርስቲያን አባላት 75 በመቶዉ ጠቅላላ ጉባኤ ስምምነት አማካኝነት ነዉ።

4.9.3 ወንጌላዊ ተጠሪነቱ ለቤተክርስቲያኒቱ ዋና መጋቢ ወይም መጋቢ በሌለበት ለመሪዎች ጉባኤ ይሆናል።

4.9.4 ወንጌላዊ ድምጽ አልባ የመሪዎች ጉባኤ አባል ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

## 4.10 የወንጌላዊ ችሎታና ብቃት

4.10.1 ራሱን ለወንጌል አገልግሎት አሳልፎ የሰጠ፡፡ዮሐንስ 10፥11፣

4.10.2 ላልዳኑ ነፍሳት የተለየ ሸክም ያለውና ወንጌልን በትጋት መመስከር የሚችል ፡፡2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥5፣ የሐዋርያት ሥራ 6፥1-5፣ የሐዋርያት ሥራ 8፥5-13)፤

4.10.3 በግለሰብ ኢቫንጀሊዝም (Personal evangelism) ለሌሎች አርአያ ሊሆን የሚችል እና ቤተ ክርስቲያን ለታላቁ ተልእኮ ብቁና ታማኝ እንድትሆን የሚተጋ (ማቴዎስ28፥19፣ 2 ጢሞቴዎስ 4፥5) ፤

4.10.4 በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ። 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥1-7፣ቲቶ 1፥6-9፣ 1ኛ ጴጥሮስ 5፥1-4፣

4.10.5 በመንፈስቅዱስ የተሞላና በቅዱሳን የተመሰከረለት አገልግሎት ያለው፡፡ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥1-5

4.10.6 ለታላቁ እረኛ ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ የሆነ፡፡1ኛ ጴጥሮስ 2፥25፣ ዕብራውያን 13፥20፣

4.10.7 የቤተ ክርስቲያንን የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅ የሚተጋ (1 ተሰሎንቄ 5፥12-13 ፣ 1 ጴጥሮስ 5፥1-3)፤

4.10.8 በቤተክርስቲያኗ የእምነት መግለጫ የሚያምንና የመተዳደሪያ ደንቡንም የሚያከብርና የሚያስከብር፡፡

4.10.9 አገልግሎት እዚህ ከመቀበሉ በፊት ቢቻል በተመሳሳይ አገልግሎት ያገለገለ፡፡

4.10.10 የወንጌላዊነት ጥሪው በሽማግሌዎች ጉባዔና እንዲሁም በምዕመናን ጉባዔ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡ 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥1-7፣ 1ኛ ጴጥሮስ 5፥1-4፣

4.10.11 ቢቻል በስነመለኮት ትምሕርት ቤት የተማረ ቢሆን ይመረጣል፡፡

## 4.11 የወንጌላዊ የስራ ዝርዝርና ሃላፊነት

4.11.1 የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ዘርፍን ይመራል፣ የአገልግሎቱን መርሃግብርና በጀት ዝግጅት ያስተባብራል

4.11.2 ወንጌልን በግልም ሆነ በጋራ ይመሰክራል፣ ለወንጌል ስርጭት ጣቢያ/አዲስ ቤተክርስቲያን ተከላ ዕገዛ ያደርጋል

4.11.3 የወንጌል ስርጭት አገልጋዮችን ስለወንጌል ምስክርነት ያሰለጥናል፣ የወንጌል ምስክርነት አገልግሎትን ያስተባብራል፣እንዲሁም ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን ማቴሪያል ያዘጋጃል

4.11.4 አዲስ ጌታን የሚቀበሉ ሰዎችን መዝግቦ ይይዛል፣ መሰረታዊ የክርስትና ትምህርት ያስተምራል ወይም መማራቸውን ይከታተላል

4.11.5 የቤተክርስቲያኒቱን አባላትንና የአገልግሎት ዘርፎችን ለወንጌል ስርጭት ስራ ይቀሰቅሳል፣ በየወቅቱ ፕሮግራም በማውጣት አፈጻጸሙን ይከታተላል

4.11.6 ቤተክርስቲያን በምታወጣው ፕሮግራም መሰረት የእግዚአብሄርን ቃል ይሰብካል ያስተምራል

4.11.7 ቢያንስ በሁለት ወር አንድ ጊዜ የአገልግሎቱን ሪፖርት ለዋናው መጋቢ ወይም መጋቢ ከሌለ ለሽማግሌዎች ጉባኤ ያቀርባል

4.11.8 ለአገልግሎት የተረከባቸውን የቤተክርስቲያኒቱን ንብረቶች በአግባቡ ይይዛል

4.11.9 በዋናው መጋቢ ወይም በመሪዎች ጉባኤ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል

## 4.12 የዝማሬ አገልግሎት መሪ

4.12.1 የአምልኮና ዝማሬ አግልግሎት መሪ ተጠሪነቱ ለቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ ወይም መጋቢ በሌለበት ለሽማግሌዎች ጉባኤ ይሆናል

4.12.2 የአገልግሎቱ ዋና አላማ ጉባኤው የእግዚአብሄርን ህልውናና ታላቅነት በመረዳት በመንፈስና በእውነት እግዚአብሄርን በዝማሬ እንዲያመልከው ማነሳሳት ነው

## 4.13 የአምልኮና ዝማሬ አገልግሎት መሪ ችሎታና ብቃት

4.13.1 በዝማሬ የማገልገል ጸጋና የሙዚቃ ተሰጥኦ ያለው

4.13.2 በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ። ፩ኛ ጢሞቴዎስ 3፥1-7፣ቲቶ 1፥6-9፣ 1ኛ ጴጥሮስ 5፥1-4፣

4.13.3 በመንፈስቅዱስ የተሞላና በቅዱሳን የተመሰከረለት አገልግሎት ያለው፡፡ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥1-5

4.13.4 ለታላቁ እረኛ ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ የሆነ፡፡1ኛ ጴጥሮስ 2፥25፣ ዕብራውያን 13፥20፣

4.13.5 የቤተ ክርስቲያንን የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅ የሚተጋ (1 ተሰሎንቄ 5፥12-13 ፣ 1 ጴጥሮስ 5፥1-3)፤

4.13.6 በቤተክርስቲያኗ የእምነት መግለጫ የሚያምንና የመተዳደሪያ ደንቡንም የሚያከብርና የሚያስከብር፡፡

4.13.7 አገልግሎት እዚህ ከመቀበሉ በፊት ቢቻል በተመሳሳይ አገልግሎት ያገለገለ፡፡

4.13.8 የአገልግሎት ጥሪው በሽማግሌዎች ጉባዔና እንዲሁም በምዕመናን ጉባዔ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡ 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥1-7፣ 1ኛ ጴጥሮስ 5፥1-4፣

## 4.14 የአምልኮና ዝማሬ አገልግሎት መሪ የስራ ዝርዝርና ሃላፊነት

4.14.1 የአገልግሎት ክፍሉን ይመራል፣ ዓመታዊና ወቅታዊ የስራ ዕቅድና የክንውን ሪፖርት ለዋናው መጋቢ ያቀርባል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል

4.14.2 የአገልግሎት ክፍሉ አባላት የመንፈስ አንድነት መጠበቅና የርስ በርስ ፍቅር እንዲኅለብት አስተዋጽኦ ያደርጋል

4.14.3 ከቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ ጋር በጋራ በመስራት ለአምልኮና ዝማሬ አገልግሎት ቡድን አባላት የተለያዩ ስልጠናዎችንና ትምህርቶችን ያዘጋጃል/ያመቻቻል

4.14.4 የአምልኮና ዝማሬ አገልግሎት ቡድን አባላት በቤተክርስቲያን መደበኛ የጸሎትና ሌሎች ፕሮግራሞች ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል

4.14.5 የአምልኮ ቡድን አባላት አንድነትና ማህበራዊ ትስስር እንዲኅለብት የሚረዱ የተለያዩ ኘሮግራሞችን ያዘጋጃል

4.14.6 የስነ ምግባር ጉድለቶች በሚታዩበት ጊዜ ከአገልግሎት ክፍሉ ኮሚቴ አባላት ጋር በጋራ በመመካከር የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል። እልባት ላልተገኘባቸው ሁኔታዎች ከመጋቢው ጋር በመሆን መፍትሄ ያፈላልጋል

4.14.7 የአምልኮና ዝማሬ አገልግሎት ቡድን ውስጠ ደንብ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

4.14.8 በአገልግሎት ክፍሉ የሚገኘው ማናቸውም የቤክ ንብረት በጥንቃቄ መያዙን ይከታተላል፣

4.14.9 አዳዲስ ዝማሬዎችን የመቀበል ስጦታ ያላቸው ወገኖች ጸጋቸው እንዲኅለብት አብሮ በመጸለይና ቃሉን በማስተማር ያበረታታል

4.14.10 ቤተክርስትያን በቂ የሙዚቃ ተጫዋቾች እንዲኖራት ዝንባሌ ያላቸውን በመለየት ስልጠና እንዲያገኙ ያመቻቻል

4.14.11 በመሪዎች ጉባኤ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል

## 4.15 ረዳት አስተዳዳሪ

4.15.1.1 በመሪዎች ጉባኤ ሥር ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ረዳት አስተዳደሪ ሊመደብ የሚችል ሲሆን ጉባኤው በሚሰጠው የሥራ ዝርዝር መሰረት አስተዳደራዊ ጠባይ ያላቸውን ስራዎች ያከናውናል፡፡

4.15.1.2 በረዳት አስተዳደርነት በሙሉ ጊዜ ተመድቦ የአስተዳደርን ጉዳይ የሚያስፈጽም የመሪዎች ጉባኤ አባል አይሆንም።

## 4.16 የረዳት አስተዳዳሪ ችሎታና ብቃት

4.16.1 በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ፣ ፩ኛ ጢሞቴዎስ 3፥1-7፣ቲቶ 1፥6-9፣ 1ኛ ጴጥሮስ 5፥1-4፣

4.16.2 ከቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት ዘርፎች ጋር በመግባባትና በመቀባበል ለመስራት ተሰጥኦ ያለው፣

4.16.3 ለታላቁ እረኛ ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ የሆነ፡፡1ኛ ጴጥሮስ 2፥25፣ ዕብራውያን 13፥20፣

4.16.4 የቤተ ክርስቲያንን የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅ የሚተጋ (1 ተሰሎንቄ 5፥12-13 ፣ 1 ጴጥሮስ 5፥1-3)፤

4.16.5 በቤተክርስቲያኗ የእምነት መግለጫ የሚያምንና የመተዳደሪያ ደንቡንም የሚያከብርና የሚያስከብር፡፡

4.16.6 አገልግሎት እዚህ ከመቀበሉ በፊት ቢቻል በተመሳሳይ አገልግሎት ያገለገለ፡፡

4.16.7 በቂ የኮምፒዩተር ችሎታ ያለውና በአስተዳደር ወይም በሂሳብ ሙያ የሰለጠነ ቢሆን ይመረጣል፡፡

## 4.17 የረዳት አስተዳዳሪ የስራ ዝርዝርና ሃላፊነት

4.17.1 ለቤተክርስቲያን የሚላኩ ደብዳቤዎችን ሁሉ እንደዓይነታቸው መመዝገብና ለሚመለከታቸው ማከፋፈል፤

4.17.2 የቤተክርስቲያን እንግዶችን የመሪዎች ጉባኤ በሚወስነው መሰረት መቀበልና መስተንግዷቸውን መከታተል፤

4.17.3 በቤተክርስቲያኗ የፋይናንስና ንብረት መመሪያ መሰረት፣ የገንዘብያዥ [Petty cash holder] እና ንብረት ሠራተኛ ሥራ ድርሻዎችን ማከናወን፣ ከፋይናንስ ኃላፊው ጋር በቅርበት መሥራት፤ በዚህም መሰረት የሚከተሉትን ሥራዎች ማከናወን፥

4.17.3.1 ማንኛውንም ጥሬ ገንዘብ ገቢ ማድረግና በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ወጪ ማድረግ፣

4.17.3.2 ፔቲ ካሹን መያዝና መከታተል፣ የፔቲካሽ ማጠቃለያ በየወሩ መጨረሻ ማዘጋጀት፣

4.17.3.3 የፔቲ ካሽ መጠን እያነስ ሲሄድ ጠይቆ እንዲሟላ ማድረግ፣

4.17.3.4 የበጀትና አጠቃቀምን የሚያሳይ ሪፖርት በየወሩ ማዘጋጀት፣ የቤተክርስቲያኒቷን ሂሳብ ለውስጥና ለውጪ ኦዲተሮች ዝግጁ ማድረግ፤

4.17.3.5 ሂሳብነክ የሆኑ የወጭና የገቢ ሰነዶችን ወስዶ በአግባቡ መያዝና በየአይነቱ መመዝገብ፤

4.17.3.6 የቤተክርስቲያን አላቂ እቃዎችን ተከታትሎ መግዛት፣

4.17.3.7 ቋሚ ንብረቶችን መዝግቦ በስፍራውም መኖራቸውንና አገልግሎት ላይ መዋላቸውን መከታተል፣

4.17.3.8 የቤተክርስቲያኗን ቋሚንብረቶች በዓመት አንድጊዜ ዓመታዊ የንብረትቆጠራ (Inventory) ማድረግ፣

4.17.3.9 ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ንብረቶች በመለየት ለሽማግሌዎች ጉባኤ ሪፖርት ማድረግ፣

4.17.4 እንደአስፈላጊነቱ የቤተክርስቲያን መሪዎች የሚጠይቁትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን።

## 4.18 የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ከሥራ መልቀቅ ወይንም የመገለል ሁኔታ

4.18.1 በቤተክርስቲያኒቱ መንፈሳዊውም ሆነ አስተዳደራዊ የአገልግሎት ዘርፍ ተቀጥሮ የሚያገለግል አገልጋይ ሙሉጊዜ አገልጋይ ይባላል

4.18.2 ማንኛውም የቤተክርስቲያኒቱ ሙሉጊዜ አገልጋይ አገልግሎቱን በፈቃዱ መልቀቅ ቢፈልግ ጉዳዩን ስራ ከሚያቆምበት ጊዜ 3 ወር ቀደም ብሎ በጽሑፍ ለመሪዎች ጉባዔ ሲያቀርብ መሰናበት ይችላል።

4.18.3 የሙሉጊዜ አገልጋይ የሞራል ውድቀት ሲገኝበት ወይም የእምነት ግድፈት ሲገኝበት ወይም የቤተክርስቲያንዋን መተዳደሪያ ደንብ ሲተላለፍ፣ ጉዳዩ በመሪዎች ጉባኤ አባላት አማካይነት ይታያል፣ የጉዳዩን ክብደት በማመዛዘን በመጀመሪያ የማስጠንቀቂያ፣ የማረሚያ፣የምክር ቃልና ደብዳቤም ይሰጠዋል፡፡ ነገር ግን

የተገኘበት ጉድለት በማስጠንቀቂያ የማይታለፍ ከሆነ ወይም ተደጋጋሚ ማስጠንቅቂያ የማይመልሰው ከሆነ ከአገልግሎቱ ተገልሎ (ተወግዶ)፣ የመሪዎች ጉባኤ ጉዳዩን ለጠቅላላ ጉባዔ በማቅረብ ያስወስናል።

4.18.4 ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የሙሉጊዜ አገልጋዩን ከሥራ ማሰናበት ካስፈለገ የ90 ቀናት ማስታወቂያ ይሰጠዋል፡፡ ቀናቱ በጠቅላላው ጉባዔ ስምምነት ሊለወጥ ይችላል፡፡

4.18.5 የጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔ በ75 በመቶ እጅ ከተደገፈ የሙሉ ጊዜ አገልጋዩ ከስራ ይገለላል።

## 4.19 የቤተክርስቲያን ሽማግሌ

4.19.1 ሽማግሌ ማለት በመንፈሳዊ ጥበብና ዕውቀት የበሰለ እንዲሁም ሌሎችን የመምራት፣ የማስተዳደር፣ ችሎታ ያለው ነው። ስለሆነም አንድ ሽማግሌ የሚከተሉትን እንዲያሟላ ይጠበቃል፤

4.19.1.1 ያለነቀፋ በጽድቅና በቅድስና የሚኖር/የምትኖር፡፡

4.19.1.2 በቃል ዕውቀት የተሞላና/የተሞላችና ማስተማር የሚችል/የምትችል፣

4.19.1.3 ቅንና በጎ ባህሪያ ያለው/ያላት፣

4.19.1.4 በሕብረተሰቡ ዘንድ መልካም ምስክርነት ያለው /ያላት፣

4.19.1.5 ትሑትና ራሱን/ራሷን የሚገዛ/የምትገዛ፣

4.19.1.6 ቤተክርስቲያኗ የቆመችለትን ዓላማ የሚደግፍ/የምትደግፍ፣

4.19.1.7 አስራቱን/አስራቷን በመክፈል ለቤተ ክርስቲያን ታማኝ የሆነ/ የሆነች።

4.19.1.8 የአንድ ሚስት ባል፣ የሚታዘዙ ልጆች ያሉት/ያሏት፣ ቤቱን በመልካም ሁኔታ የሚያስተዳድር/የምታስተዳድር።

4.19.1.9 ቀደም ሲል በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው፣ጊዜአቸውንና ጉልበታቸውን እንዲሁም እግዚአብሔር የሰጣቸውንም ጥበብ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ለማዋል ፈቃደኞች የሆኑና ከዚህም ሌላ የእግዚአብሔርን ቃል መስፈርት የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

4.19.1.10 በዚሁ ቤተክርስቲያን ቢያንስ ለ2 ዓመት ያህል አባል የሆነ/የሆነች።

## 4.20 የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አመራረጥ

4.20.1 የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ቁጥር እንደ አስፈላጊነቱ አራት ወይም ስድስት ይሆናል።

4.20.2 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ቁጥር አምስት ይሆናል። በመሪዎች ጉባኤ በጥቆማ ቀርበው በአጠቃላይ አባላት ጉባኤ ምርጫቸዉ ይጸድቃል። የሽማግሌዎችም መስፈርት በጽሑፍ ተሰጥተዋቸው ሥራቸውን ያከናውናሉ።

4.20.3 የመሪዎች ጉባኤ አባላትና የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት በጋራ በመጸለይና በመመካከር የሚፈለገውን እጥፍ ተመራጭ እጩ ሽማግሌዎችን ይለያሉ።

4.20.4 እጩ ሽማግሌዎች ፈቃደኝነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ በአስመራጭ ኮሚቴ አማካኝነት ለቤተክርስቲያን ጉባኤ አባላት እንዲቀርቡ ይደረግና የሽማግሌዎች ምርጫ ይካሄዳል።

4.20.5 እያንዳንዱም አባል ምርጫውን በግል በጽሑፍ ያከናውናል።

4.20.6 ተመራጮች በሚያገኙት ድምፅ ቅደም ተከተል መሰረት አስፈላጊው ቁጥር ተወስዶ ተግባራዊ ይሆናል

4.20.7 የምርጫው ውጤት በአስመራጭ ኮሚቴ አማካኝነት በምርጫው ዕለት ወዲያውኑ ይገለፃል፡፡

4.20.8 ከነባር ሽማግሌዎች ሁለት አባላት ለሚቀጥለው የአገልግሎት ዘመን በቀጥታ እንዲያልፉ ይደረጋል። እነዚህም እንደ አስፈላጊነቱ በመሪዎች ጉባኤ በድምጽ ብልጫ ይመረጣሉ፡ ለዚህም ፈቃደኝነታቸዉ ይጠየቃል።

## 4.21 የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የአገልግሎት ዘመን

4.21.1 የሽማግሌዎች የአገልግሎት ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል፡፡

4.21.2 አንድ ሽማግሌ የሦስት ዓመት የአገልግሎት ዘመን ሳይጨርስ ከሀገር ቢለቅ ወይም በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱን ቢተው፣ የመሪዎች ጉባኤ በምትኩ ሌላ ሰው መምረጥ ይችላል፡፡ መርጠው ለአባላት ጉባኤ እንዲጸድቅ ያቀርባሉ፡፡ የተቃውሞ ሀሳብ ካለ አስተያየት ለመቀበል የአንድ ሳምንት ጊዜ ይሰጣል፡፡

4.21.3 የመሪዎች ጉባኤ አባል የሆነ ሰው በድጋሚ ለምርጫ ቀርቦ በመመረጥ ሊያገለግል ይችላል፡፡ አገልግሎቱም እስከ ሁለት ተርም ሊቀጥል ይችላል።

4.21.4 ሁለት ተርም በተከታታይ ያገለገለ/ች ሽማግሌ፣ቢያንስ አንድ ዓመት ከአገልግሎት ሳያርፍ በሽማግሌነት ማገልገል አይችልም።

## 4.22 የሽማግሌዎች ከስራ መልቀቅ ወይም የመገለል ሁኔታ

4.22.1.1 የቤተክርስቲያን ሽማግሌ የሞራል ውድቀት ሲገኝበት ወይም የእምነት ግድፈት ሲገኝበት ወይም የቤተክርስቲያንዋን መተዳደሪያ ደንብ ሲተላለፍ፣ ጉዳዩ በተቀሩት በመሪዎች ጉባኤ አባላት አማካይነት ይታያል፣ የጉዳዩን ክብደት በማመዛዘን በመጀመሪያ የማስጠንቀቂያ፣ የማረሚያ፣የምክር ቃልና ደብዳቤም ይሰጠዋል፡፡ ነገር ግን የተገኘበት ጉድለት በማስጠንቀቂያ የማይታለፍ ከሆነ ወይም ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ የማይመልሰው ከሆነ ሽማግሌው ከአገልግሎት ተገልሎ ጉዳዩን የመሪዎች ጉባኤ ለምዕመናን ጉባዔ በማቅረብ ይስወሰናል፡፡

4.22.1.2 ማንኛውም የመሪዎች ጉባኤ አባል በፈቃደኝነት ሥራውን መልቀቅ ቢፈልግ ይህንኑ በመጥቀስ ጉዳዩን በጽሑፍ ለመሪዎች ጉባኤ ሲያቀርብ ሙብቱ ተጠብቆ ይሰናበታል።

# 5. የገቢ ምንጭ

5.1.1 የቤተክርስቲያንዋ ገቢ ምንጭ ከምዕመንዋ የሚሰበሰበው አሥራት፣ መባና ልዩ ልዩ ስጦታዎች እንዲሁም ከመንግስት የሚገኝ ድጎማ ሁሉ ይሆናል፡፡በተጨማሪም ከባንክ ወለድ የሚገኘውንም ገቢ ያጠቃልላል። ሌሎች የገቢ ምንጮችንም ያካትታል

5.1.2 ቤተክርስቲያንዋ በየጊዜው ስለአሥራትና መባ መስጠት ለምዕመኑ ተገቢውን ትምህርት ትሰጣለች::

# 6. አባልነት

## 6.1የቤተክርስቲያኗ አባል ለመሆን የሚያበቁ ነጥቦች

6.1.1.1 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝ አምኖ የተቀበለ/ ለች፣

6.1.1.2 በሕይወቱ ወይም በአኗኗሩ ክርስቶስን መመስከር አይነተኛ ግቡ የሆነ /ች፣

6.1.1.3 የቤተክርስቲያኒቱን የእምነት አንቀጽና  መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለ፣

6.1.1.4 የቤተክርስቲያኗን የአባልነት ቅጽ ሞልቶ /ታ ያስረክባል / ታስረክባለች፣

6.1.1.5 በስራም ሆነ በሌላ ምክንያት ከሌላ ቦታ ተዛውረው ለአባልነት የሚያመለክቱ ወገኖች ስለአገልግሎታቸው፣ ስለመንፈሳዊ ህይወታቸውና ስለተከታተሉት መንፈሳዊ ትምህርት የሚያስረዳ መሸኛ ደብዳቤ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል

6.1.1.6 ወላጆቻቸው የቤተክርስቲያኗ አባላት የሆኑ ወጣቶች እና ልጆች እድሜአቸው ለመምረጥ እስኪደርስ የቤተክርስቲያኗ አባል ተደርገው ይቆጠራሉ።

## 6.2 የአባላት ኃላፊነት

6.2.1.1 በቤተክርስቲያኗ የእምነት መግለጫ የሚያምን፣ እርስ በርስ መተሳሰብ፣ በመደጋገፍ፣ በክርስቶስ ዕውቀት፣ በቅድስናና በመሸካከም በፍቅር መቆም፣

6.2.1.2 በዓለም ውስጥ በንፅህና በመመላለስና በኑሮአችን በምስክርነታችን ነፍሳትን ወደኢየሱስ ክርስቶስ ለመሳብ መጣር እንዲሁም በንግግራችን፣ በፍቅራችን፣ በእምነታችን፣ በሕይወታችንም ንፅህና የክርስቶስ ምሳሌ ለመሆን መጣር፣

6.2.1.3 በሕብረት መሰባሰባችንን ሳንዘነጋ የእርስበርስ መንፈሳዊ ግንኙነት በማጠናከር፣አብሮ ጌታን ማምለክና ቃሉን ማጥናት፣

6.2.1.4 በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የተመረጡትንና የተጠሩትን አገልጋዮች ማክበርና መደገፍ፣ መንከባከብ፡፡

6.2.1.5 አስራቱን/አስራቷን በመክፈል ለቤተ ክርስቲያን ታማኝ መሆን፣

6.2.1.6 አቅም በፈቀደ መጠን በሃብታችንና በንብረታችን መርዳት፡፡ በመሀከላችንም ቃሉ የሚያድግበትና የሚሠራጭበትን መንገድ መፈለግ፤ እንዲሁም በተሰጠን የተለያዩ እውቀትና ችሎታ በቤተክርስቲያኒቷ አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ ይሆናል፡፡

6.2.1.7 በአባላት ስብሰባ ወቅት መሳተፍ፣ እንዲሁም በሽማግሌዎች ምርጫ መሳተፍ።

## 6.3 ስለ ዲሲፕሊን

6.3.1.1 ቤተክርስቲያን በአባሎቿ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ የምትወስደው ጉድለት የተገኘበት አባል ከጥፋቱ ታርሞ እንዲመለስና ክርስቲያናዊ ሥነምግባር ያለውን ሕይወት እንዲመራ ለማድረግ ነው።

6.3.1.2 የዲሲፕሊን እርምጃ ከሚያስወስዱ ጉዳዮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፣

6.3.1.3 ለቤተክርስቲያን ሥልጣን ባለመገዛት አመጽን ማካሄድ፣

6.3.1.4 በዝሙት ሐጥያት መገኘትም ሆነ መኖር፣ለምሳሌ ቃልኪዳን ሳይፈጽሙ አብረው መኖር፣

6.3.1.5 እንደ እግዚአብሔር ቃል ከሆነ በቂ ምክንያት ዉጭ ትዳርን ማፍረስ፣

6.3.1.6 በቤተክርስቲያን አባላት መካከል ቅራኔ ሲፈጠር በይቅርባይነት ለመታረቅ ፍቃደኛ አለመሆን፣

6.3.1.7 ቤተክርስቲያንን የመከፋፈል ድርጊት መፈፀም፣

6.3.1.8 በቤተክርስቲያን ውስጥ የስሕተት ትምሕርት ማስፋፋት፣

6.3.1.9 እንዲሁም በሽምግልና ጉባኤው አመለካከት የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስወስድ የሚችል ሌሎች ተግባራት ሲፈጽሙ።

## 6.4 በአባላት ላይ የዲሲፕሊን ርምጃ ስለመውሰድ

6.4.1 የመሪዎች ጉባኤ በአባላት ውስጥ ለሚፈጸሙ የሥነሥርዓት ጉድለቶች እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢውን የሥነሥርዓት እርምጃ ይወስዳል፡፡

6.4.2 አንድ የቤተክርስቲያኗ አባል በቁ 6.3 በተጠቀሰው መሠረት ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር የጎደለው ተግባር ፈጽሞ ቢገኝ እንደ እግዚአብሔር ቃል የመሪዎች ጉባኤ በተጠያቂው አባል ላይ ተገቢ የሆነውን የዲሲፕሊን ርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው፡፡ ሆኖም የሚወሰደው የሥነሥርዓት ርምጃ ፍቅር የተላበሰ ሆኖ ተጠያቂውን አባል ለወደፊት ለማረምና ለማስተካከል እንጂ አባሉን ለመጉዳት አይሆንም፡፡አባሉ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ የሚከተለው ርምጃ በቅደም ተከተል ይወሰድበታል፡፡

6.4.2.1 የቃል ምክር ይሰጠዋል፣

6.4.2.2 የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣

6.4.2.3 ከቤተክርስቲያን አባልነት እንደ አስፈላጊነቱ ለተወሰነ ጊዜ ሊገለል ይችላል፣

6.4.3 ከላይ በተጠቀሱት ከንዉኖች አንድ አባል የንስሓ ፍሬ ካላሳየ ከቤተክርስቲያን ሊታገድ ይችላል።አንድ አባል በዚህ ሁኔታ ዉስጥ ሲገኝ፣የንስሃ ፍሬ ለማሳየት ይበቃ ዘንድ ቤተክርስቲያን የመከታተልና የመደገፍ የማስተማርም ሃላፊነት አለባት።

6.4.4 ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው አባል አገልጋይ ከሆነ እላይ የተጠቀሱት በአባልነቱ የሚመለከቱት ሆኖ፣ በተጨማሪም ምሳሌ የመሆን ድርብ ሃላፊነት ስለሚጠበቅበት፣ የመሪዎች ጉባኤ እንደጥፋቱ ሁኔታ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ከአገልግሎት ሊታገድ ይችላል።ይህም እስከ ሁለት ዓመት ሊደርስ ይችላል።

## 6.5ከአባልነት የመልቀቅ ወይንም አባልን ከአባልነቱ የማስወገድ ደንብ

አንድ አባል ከአባልነት የሚለቀው ወይም የሚገለለው፣

6.5.1 በፈቃደኝነት ከአባልነት ለመሠረዝ ወይም ለመውጣት ሲፈልግ፣

6.5.2 በመሪዎች ጉባኤ የሥነሥርዓት ርምጃ ሲወሰድ ብቻ ነው፡፡ ይህ ውሳኔ ለጠቅላላ ጉባኤው ይገለፃል፡፡ ይህም የሚደረገው ግለሰቡ ከተሰማራበት ስሕተት ጉባዔው እንዲጠበቅ ለማድረግ ነው፡፡

## 6.6ወደ አባልነት መመለስ

6.6.1 ከአባልነት የተገለለ ግለሰብ እንደገና ለመመለስ በሚያመለክትበት ወቅት የመሪዎች ጉባኤ ነገሩን አጥንቶ ሲወሰን ጠቅላላጉባዔው እንዲያውቀው ይደረጋል።

## 6.7የምእመናን ጠቅላላ ጉባኤ የሚመለከት

6.7.1 በዓመት ሁለት ጊዜ የቤተክርስቲያኒቷ አባላት በመሰብሰብ በዓመቱ ውስጥ የተሰሩትን ሥራዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮችን፣ የተወሰደ መፍትሄዎችን፣ወደፊት ሊደረጉ ያሉትን የሥራ ዕቅዶች ከተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ተ ጠሪዎች በሪፖርት መልክ ይሰማል፡፡

6.7.2 በስብሰባው ወቅት የመሪዎች ጉባኤ ሰብሳቢ በአስተባባሪነት ሲገኝ የመሪዎች ጉባኤ ጸሐፊ የስብሰባው ጸሐፊ በመሆን ይገለግላል፡፡

## 6.8የምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ የሥራ ኃላፊነትና ተግባር

6.8.1 ምዕመኑ የሚደረገውን የክህነት ሥርዓት ማለትም የመጋቢዎችን ክህነትና እንዲሁም የሽማግሌዎችን ምርጫ ያረጋግጣል፡፡ይህም ሥርዓት የሚፈጸመው ሕጋዊነቱም የሚታወቀው ምልዓተጉባዔ ሲሞላ ብቻ ነው፡፡

6.8.2 ምዕመኑ ከመጋቢው፣ ከሽማግሌዎች፣ ከሌሎችም አገልጋዮች ጋር በጸሎት በፍቅርና በማክበር ይተባበራል፡፡

6.8.3 መጋቢውና የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የሚያወጡትን ወይም የሚያስተላልፉትን መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

6.8.4 በድምጽ ብልጫ የሚወሰን ነገር ቢኖር ድምጽ በመስጠት ይወስናል፡፡

6.8.5 ቋሚ የቤተክርስቲያን ንብረት (ለምሳሌ ህንጻ፣ መሬት ወዘተ) ወይም ግምታቸው ከ100000 (መቶ ሺህ) ክሮነር በላይ የሚያወጡ እቃዎች ለመሸጥ፣ለመግዛት ወይም ለመለወጥ የሚደረገው ስምምነት በጠቅላላ የአባላት ስብሰባ ወቅት ይወሰናል፡፡

## 6.9 ክፍያ

6.9.1 ቤተክርስቲያኗ የሙሉጊዜ አገልጋዮች ለኑሯቸው የሚያስፈልጋቸውን ተገቢ መተዳደሪያ የቤተክርስቲያኗ አቅም በሚችለው መጠን ተገቢው ክፍያ እየተከፈላቸው ያገለግላሉ። የመሪዎች ጉባኤ አባላትና ሌሎች አገልጋዮች ግን ያለክፍያ ያገለግላሉ፡፡

# 7. ደንቡን የማሻሻል ይዘት

7.1.1 በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ላይ የሚቀርብ ማንኛውም የማሻሻያ ሀሳብ ቢኖር በመሪዎች ጉባኤ ሶስት አራተኛ ድምጽ ከታመነበት እንዲጸድቅ ወደ አባላት ጉባኤ ይቀርባል፡፡ የማሻሻያ ሀሳቡ በአባላት ጉባኤ ከጸደቀ በኋላ ስራ ላይ ይውላል፡፡